
ህግህ ለእግሬ መብራት
የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት
ከዘፍጥረት - ዘዳግም
አምስቱ የሙሴ መጻሕፍት
ክፍል አንድ
ከአድነው ተሾመ 1993 ዓ.ም

# ሕግህ ለእግሬ መብራት

ከአድነው  ተሾመ

1993 ዓ.ም.

## የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት

ከዘፍጥረት እስከ ዘዳግም

(አምስቱ የሙሴ መጻሕፍት)

## ክፍል አንድ

ይህንን መጽሐፍ ያ ደራሲው ፈቃድ በሙሉ
ወይም በከፊል ማባዛት ወይም መልሶ ማሳተም በሕግ
የተከለከለ ነው 1993 ዓ.ም

**Copyright 2001, Adnew Teshome**

# ምዕራፍ ሁለት

## ዘፍጥረት

ዘፍጥረት የነገሮች ሁሉ <u>መጀመሪያና መሠረት</u> ያለበት መጽሐፍ ነው:: በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ያሉ የተስፋ ቃሎች፣ መገለጦችና መልዕክቶች ሁሉ መሠረታቸው (መነሻቸው) በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ በዘፍጥረት ውስጥ ነው:: ዘፍጥረት የመጽሐፍ ቅዱስ ሥር (መሠረት) ነው፤ ብሉይ ኪዳን የዛፉ ግንድ ነው፤ አዲስ ኪዳን ደግሞ ቅርንጫፉና ፍሬው ነው:: ወንጌልም በመጀመሪያ የሚገኘው በዘፍጥረት ውስጥ ነው:: «... በአንተ አሕዛብ ሁሉ ይባረካሉ ብሎ ወንጌልን ለአብርሃም አስቀድሞ ሰበከ» (ገላ. 3፥8፤ ዘፍ. 12፥3:): የመጀመሪያው የወንጌል የተስፋ ቃል የሚገኘው በዘፍጥረት ነው:: ዘፍ. 3፥15::

ደራሲው: - ሙሴ እንደሆነ ይታመናል::

የነገርን (የፍጥረትን) ሁሉ ሥር የያዘ ነው:: የዘፍጥረት ዋና መልዕክት የእግዚአብሔር ሁሉን ቻይነት ከሃሊነት ነው::

### ከዘፍጥረት- ዘዳግም በአጭሩ

| የመጽሐፉ ስም | በሰው በኩል ሲታይ | በእግዚአብሔር በኩል ሲታይ |
|---|---|---|
| ዘፍጥረት | የሰው ኃጢአትና ውድቀት | የእግዚአብሔርን ከሃሊነት (ሁሉን ቻይነት) እና ሉአላዊነት ያሳያል በዘፍጥረትና በመጥራቱ |
| ዘጸአት | ከባርነት ነጻ መውጣት የበግ ደም በመቃኑ ተቀብቶ (ፋሲካ) | የእግዚአብሔርን ኃይል ያሳያል፣ ከግብፅና ከፈርዖን እሥራት ነፃ የሚያወጣ |
| ዘሌዋውያን | እንደ እግዚአብሔር ሕዝብ የመኖር ሥርአት (ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት) | የእግዚአብሔርን ቅድስና ያሳያል (እኔ ቅዱስ ነኝና እናንተም ቅዱሳን ሁኑ) |
| ዘኍልቁ | በምድረ በዳ የመባዘን (የአለመታዘዝ) ዘመን ከእግዚአብሔር ምሪት በበረሃ | የእግዚአብሔርን ቸርነትና ፍርድ ያሳያል 1ቆሮ. 10፣1-11 |
| ዘዳግም | የጉዞው መጨረሻ (ግምገማ) | የእግዚአብሔርን ታማኝነት ያሳያል ህዝቡን ዳር በማድረስና የተስፋውን ቃል በመጠበቅ ዘዳ. 6፣23 |

# ዘፍጥረትና ራእይ

| ዘፍጥረት | ራእይ |
|---|---|
| ⟵ ዘላለም⟶ መጀመሪያ ——— | ——— መጨረሻ ⟶ ዘላለም |
| ዘላለም | |

### ተመሳሳይነታቸው
### (በተለይ ከውድቀት በፊት ያለው ክፍልና ራእይ)

| | | ዘፍጥረት | ራእይ |
|---|---|---|---|
| 1. | አዲስ ጅማሬ | ዘፍ. 1፥1 | ራእ. 21፥1 |
| 2. | የሕይወት ዛፍ | ዘፍ. 3፥22 | ራእ. 22፥2 |
| 3. | አዲስ ሙሽራ | ዘፍ. 2፥18-24 | ራእ. 19፥7<br>ራእ .22፥17 |
| 4. | እግዚአብሔር ከሰው ጋር ሲመላለስ | ዘፍ. 3፥8 | ራእ፤ 21፥3 |
| 5. | እግዚአብሔር ለሰው ያለው ምኞትና ዕቅድ | ዘፍ. 1፥28 | ራእ. 22፥5 |

### ልዩነታቸው

| | ዘፍጥረት | ራእይ |
|---|---|---|
| 1. | ገነት ለሰው ተዘጋች (ዘፍ. 3፥23) | ገነት ለሰው ተከፈተች (ራእ. 21፥2) |
| 2. | ሰው በኃጢአት ከእግዚአብሔር ተለየ (ዘፍ. 3፥8) | በክርስቶስ ደም ከእግዚአብሔር ጋር ታረቅን (ራእ. 1 ፥5-6) |
| 3. | እርግማን ወደ ዓለም ገባ (ዘፍ. 3፥17 3፥) | እርግማን ከዓለም ወጣ (ራእ. 22፥3) |
| 4. | ሰው ከሕይወት ዛፍ እንዳይበላ ተከለከለ (ዘፍ 3፥22) | የሕይወት ዛፍ ለሰው ተፈቀደ (ራእ. 2፥7) |
| 5. | ኃዘን፣ ሞትና፣ መከራ ገባ (ዘፍ. 3፥17፤3፥8፥4፥8) | ኃዘን፣ ሞትና መከራ አበቃ (ራእ. 21፥4) |
| 6. | ሰይጣን በሽንገላ የሰውን ሥልጣን ወሰደ (ዘፍ. 3 በሙሉ) | ሰው የተወሰደበትን ሥልጣን መልሶ አገኘ (ራእ. 22፥3-5) |
| 7. | የነገር ሁሉ ጅማሬ ነው (ዘፍ. 1፥1) | የነገር ሁሉ ፍጻሜ (ራእ. 21፥4) |

በዘፍጥረት የተጀመረ በራእይ ፍጻሜ አገኘ

| | ዘፍጥረት | ራዕይ |
|---|---|---|
| 1. | ሞት ጀመረ የመንፈስ ሞት (ዘፍ. 3፣8) የሥጋ ሞት( ዘፍ. 5፣5) | ሁለተኛው ሞት የዘላለም ስቃይ (ራእይ 20፣14-15፤ 21፣8) |
| 2. | በሰይጣን ላይ ቅጣት ተላለፈ (ዘፍ. 3፣15) | ቅጣቱ ተፈፀመበት (ራእ. 20፣10) |
| 3. | የመሲህ ተስፋ ተሰጠ (ዘፍ. 3፣15) | የመሲሁ ተስፋ ተፈጸመ (ራእ. 1፣5-6) |

## ዘፍጥረት ለሁለት ይከፈላል

፩. <u>የቅድመ ታሪክ ዘመን</u> - ከምዕ. 1-ምዕ. 11 አራት ጎልተው የሚታዩ ድርጊቶች አሉ

1. ፍጥረት: - የእግዚአብሔር ሉአላዊነት- በግዑዙ አለም
2. የአዳምና ሔዋን በኃጢአት መውደቅና ከገነት መባረር . .የእግዚአብሔር ሉአላዊነት- በሰው ላይ
3. የውኃ ጥፋት: - የእግዚአብሔር ሉአላዊነት: - በታሪክ ላይ
4. የባቢሎን ግንብ: - የእግዚአብሔር ሉአላዊነት በሰው መንግሥት (አስተዳደር) ላይ

፪. <u>የእምነት አባቶች:</u> - ከምዕ. 12-ምዕ 50

1. አብርሃም- መለኮታዊ ጥሪ (ዘፍ. 12÷1)
   አብርሃም የሚታወቀው በእግዚአብሔር <u>በመታመን</u> ነው (ዘፍ. 15÷6)
2. ይስሐቅ- መለኮታዊ ልደት (ዘፍ. 21÷2)
   ይስሐቅ የሚታወቀው <u>በመታዘዙ</u> ነው (ዘፍ.22÷7-10)
3. ያዕቆብ -መለኮታዊ ጥበቃ (ዘፍ. 48፣16)
   ያዕቆብ የሚታወቀው <u>ለበረከት በመታገሉና</u> (<u>በአገልግሎቱ</u>) ነው (ዘፍ. 32÷24-30)
4. ዮሴፍ:- መለኮታዊ ምሪት (ዘፍ. 50÷20)
   ዮሴፍ የሚታወቀው <u>በመጽናቱ</u> ነው (መዝ. 105÷17-19)

<u>በዘፍጥረት ስለ ሰው ሦስት ነገሮችን እናስተውላለን</u>

1. ሰው በኃጢአት የተበላሸ ዘፍ. 3 በሙሉ (ዘፍ. 1፥26-28፣ መክ. 7፥29)
2. ሰው በኃጢአት ተበላሸ (ዘፍ. 3 በሙሉ)
3. ሰው የመታደስ ተስፋ ተሰጠው (ዘፍ. 315፣ ዘፍ. 12፥2-3)

<u>ዘፍ. 1፥1ን እንመልከት</u>

«በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ » (ዘፍ. 1፥1)፡፡

«በመጀመሪያ እግዚአብሔር»

እነዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ የመጀመሪያ ሁለት ቃላት ለሰው ችግር በሙሉ መፍትሔ የሚሆንን መልእክት ያስተላልፋሉ፡፡

እግዚአብሔር በመጀመሪያ ካስቀደምነው፤ ነገሮች በሙሉ መልክ ይይዛሉ፡፡

«አስቀድማችሁ የእግዚአብሔርን መንግሥት ጽድቁንም እሹ ሌላውም ሁሉ ይጨምርላችኋል» (ማቴ. 6፥33)፡፡

<u>ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ የመጀመሪያ ጥቅስ የተለያዩ የሰውን የተሳሳቱ ፍልስፍናዎች ያፈራርሳል</u>

1. እግዚአብሔር የለም (ኢአማኒት)- «በመጀመሪያ እግዚአብሔር»
2. ብዙ አማልክት አሉ (እግዚአብሔር ብዙ ነው) - «በመጀመሪያ እግዚአብሔር» ነጠላ ቁጥር
3. ነገሮች በሂደት (በEvolution) የመጡ እንጂ የተፈጠሩ አይደሉም «በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን <u>ፈጠረ</u>»
4. እግዚአብሔርና ፍጥረት አንድ ናቸው - ሁሉ አምላክነት (Pantheism) «በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ» እግዚአብሔር «ፈጣሪ» ፍጥረት ደግሞ «ፍጡር» ነው፡፡
5. ከሚታየው ዓለም ውጭ ሌላ ዓለም (ቁስ አካልነት) /Matrerialism/ «በመጀመሪያ እግዚአብሔር ከማይታየው ዓለም ሰማይና ምድርን (የሚታየውን ዓለም) ፈጠረ»

6. ሁሉ ነገር የራስን ዕድል ፈንታ ተከትሎ የሚሆን ነው (Fatalism) «በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይና ምድርን ፈጠረ» በዕድል የተገኘ ሳይሆን በዓላማ የተፈጠረ ነው።

<u>የዘፍ. 1፥1 እና 1፥2 ልዩነት</u>

«በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ። ምድርም ባዶ ነበረች አንዳችም አልነበረባትም፤ ጨለማም በጥልቁ ላይ ነበረ፤ የእግዚአብሔርም መንፈስ በውኃ ላይ ሰፍፎ ነበረ።»

የመጽሐፍ ቅዱስ አዋቂዎች እንደሚሉት በቁ. 1 እና 2 መካከል የብዙ ዘመናት ልዩነት አለ። ቁጥር 1 ስለ መጀመሪያው አፈጣጠር ሲናገር ቁጥር 2 ደግሞ ምድር ከተፈጠረች በኋላ ባዶ እንድትሆን ያደረጋት ነገር እንደ ነበረ ያመለክታል ይላሉ። በኢሳ. 45፥18 «ሰማያትን የፈጠረ እግዚአብሔር እርሱም <u>ምድርን የሠራና ያደረገ ያጸናትም መኖሪያም ልትሆን እንጂ ለከንቱ እንድትሆን ያልፈጠራት</u> አምላክ እንዲህ ይላል፤» የሚል ቃል እናነባለን።

ስለዚህ ምድር ስትፈጠር ለመኖሪያነት እንጂ ባዶ (ከንቱ) እንድትሆን እንዳልተፈጠረች እናያለን።

ከእነዚህ ጥቅሶች፣ ምድር ባዶ እንድትሆን ሳይሆን ለመኖሪያ እንደተፈጠረችና በአንድ በተወሰነ ወቅት ባዶ (ከንቱ) እንድትሆን ያደረጋት ነገር እንደተከሰተ እንረዳለን በተጨማሪም በኤር. 4፥23-27 ነቢዩ ኤርምያስ ምድርን ባዶ ሆና እንዳያትና አንዳችም እንዳልነበረባት በመግለጽ ልክ ዘፍ. 1፥2 ላይ ያለውን ሁኔታ ይገልጻል። ይህም የሆነው ከእግዚአብሔር ጽኑ ቁጣ የተነሣ እንደሆነ ይናገራል።

ምድር መልካም ሆና ለመኖሪያ ከተፈጠረች እንዴት ባዶና አንዳች ያልነበረባት እንዲሁም በጨለማ የተዋጠች ሆነች ብለን ስንጠይቅ ምናልባት መልስ የሚሆነን ሐሳብ በኢሳ. 14፥9-17 እና ሕዝ. 28፥11-18 እናገኛለን። እነዚህም ክፍሎች ሉሲፈር እንዴት ከነበረበት የክብር ቦታ በትዕቢቱ ወደ ምድር እንደተጣለ የሚያስረዱ ናቸው።

ኢሳ. 14፥12 «አንተ የንጋት ልጅ አጥቢያ ኮከብ ሆይ፥ እንዴት ከሰማይ ወደቅህ? ... እንዴት <u>እስከ ምድር ድረስ ተቆረጥህ?...»</u>

ኢሳ. 14፥20 «<u>ምድርህን</u> አጥፍተሃልና ...»

ሕዝ. 28÷17 «... በምድር ላይ ጣልሁህ...»
ሕዝ. 28÷18 «... በሚያዩህም ሁሉ ፊት በምድር ላይ አመድ አድርጌሃለሁ።»

እነዚህን ሐሳቦች በአንድነት በምናይበት ጊዜ እግዚአብሔር ምድርን ለመኖሪያ ከፈጠራት በኋላ የሉሲፈር ወደ ምድር መጣል በምድር ላይ ጥፋትን ያመጣ ይመስላል።

በዘፍ. 1 «ፈጠረ» የሚለው ቃል በዕብራይስጥ "Bara"
በቁ.. 1፣ በቁ. 21 እና በቁ. 27 ላይ ብቻ ይገኛል። ሌላው
ሁሉ የምድርን መደራጀት መሠራት ነው የሚያሳየው።

ቁ. 3 -«ብርሃን ይሁን አለ»
ቁ. 6- «ጠፈር ይሁን ... ይከፈል»
ቁ. 9- «ውኃ .. ይሰብሰብ የብሱም ይገለጥ።»
ቁ. 11 «ምድር ... ሣርን .. ቡቃያን ... ዛፍን ታብቅል»
ቁ. 14 -«ብርሃናት በሰማይ ጠፈር ይሁኑ»
ቁ. 16- ብርሃናትን አደረገ»

እነዚህ ቃላት ሁሉ ያለን ነገር ማደረጀትን እንጂ የሌለን ነገር መፍጠርን አያመለክቱም።

ፈጠረ የሚለው ቃል የተጠቀሰው፤

በቁ.1 - «በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ»
በቁ.. 21- «ሕያዋን ፍጥረታትን ሁሉ ... ፈጠረ»
በቁ. 27- «እግዚአብሔርም ሰውን በመልኩ ፈጠረ»

## ዘፍጥረት ምዕራፍ አንድና ሁለት፤

- ስለ ሥነ-ከዋክብት ምርምር (**Astrology**)፤

ዘፍ. 1÷14 «እግዚአብሔርም አለ፤ ቀንና ሌሊትን ይለዩ ዘንድ ብርሃናት በሰማይ ጠፈር ይሁኑ፣ ለምልክቶች፣ ለዘመኖች ለዕለታት ለዓመታትም ይሁኑ»

ፀሐይ፣ ጨረቃና ከዋክብት፣ ለምልክቶች፣ ለዘመናት፣ ለዕለታትና ለዓመታት መለያ እንደሚያገለግሉ ያሳያናል። በሥነ-ክዋክብት ምርምር የከዋክብትን ክምችቶች እያጠኑ ብዙ ነገር

እንደሚናገሩ ሁሉ የእግዚአብሔር ቃል አስቀድሞ እነዚህ ብርሃት «ለምልክቶችም» እንደሚሆኑ ተናግሮአል። በአዲስ ኪዳን ሰብዓ ሰገል ኮከብ እየተከተለ ወደ ኢየሱስ እንደመጡ እናነባለን (ማቴ. 2÷1-12)

በመጽሐፈ ኢዮብም እግዚአብሔር ኢዮብን እንዲህ እያለ ይጠይቀዋል፡፡

«በውኑ የሰባቱን ከዋክብት ዘለላ ታስር ዘንድ ወይስ ኦሪዮን የሚባለውን ኮከብ ትፈታ ዘንድ ትችላለህን? ወይስ ማዞሮት የሚባሉትን ከዋክብት በጊዜአቸው ታወጣ ዘንድ፣ ወይስ ድብ የሚባለውን ኮከብ ከልጆቹ ጋር ትመራ ዘንድ ትችላለህን? <u>የሰማይን ሥርዓት ታውቃለህን? በምድርስ ላይ እንዲሰለጥን ልታደርግ ትችላለህን?»</u> ኢዮ. 38÷31-33)

ሁሉ <u>እንደ ወገኑ</u> እንደተፈጠረ፤

በዘፍ.1÷21-25 እግዚአብሔር እንስሳትን ሲፈጥር እያንዳንዱን እንስሳ እንደ ወገኑ እንደ ፈጠረ ይናገራል፡፡ እጽዋቶችም እንደዚሁ (ቁ.12)፡፡ አዝጋሚ ለውጥ (Evolution) እንደሚለው አንዱ ወገን( ☒⑦☙☙⓪☙⑩) ከእርሱ ከሚያንስ ወገን ተሻሽሎ የመጣ ሳይሆን÷ እያንዳንዱ ወገን ውብ ሆኖ የተሠራና የራሱን መስመር ይዞ የሚሄድ ልዩ ፍጥረት ነው፡፡ እስከ አሁን ድረስ ከአንዱ ወገን ወደ ሌላው ወገን እንደ ሰንሰለት የሚያያዝ ማዕከላዊ ወገን እንዳልተገኘ ሊቃውንት እራሳቸው ይናገራሉ፡፡ ሰንሰለቱ ያልተገኘው እግዚአብሔር ከጅምሩ እያንዳንዱ <u>እንደ ወገኑ</u> አድርጎ ስለፈጠረው ነው፡፡

<u>ሰው የፍጥረት ሁሉ አውራ እንደሆነ፤</u>

እግዚአብሔር ሰውን ሲፈጥር ምድርንና በምድር ላይ ያለውን ሁሉ እንዲገዛ አድርጎ ነው፡፡ (ዘፍ. 1÷26-28)

መዝሙር ዳዊት ምዕራፍ ስምንትም ሰው የፍጥረት ሁሉ አውራና ገዥ ሆኖ እንደተፈጠረ ይናገራል፡፡ በኋላ ግን ሰው በእባብ (በሰይጣን) ተሸንግሎ የተሰጠውን ሥልጣን ለሰይጣን እንዳስረከበ በዘፍጥረት ምዕራፍ 3 እናነባለን፡፡ በሉቃ. 4÷5-6 ዲያብሎስ ኢየሱስን «... ረጅም ወደሆነ ተራራ አውጥቶ የዓለምን መንግሥታት ሁሉ በቅጽበት አሳየው፡፡ ዲያብሎስም÷ <u>ይህ ሥልጣን ሁሉ ክብራቸውም ለእኔ ተሰጥቶአል</u>.. ብሎ ሲፈትነው እናያለን፡፡ ዲያብሎስ «ይህ ሥልጣን ሁሉ ክብራቸውም ለእኔ ተሰጥቶአል» ብሎ የተናገረው ቃል ሐሰት ቢሆን ኖሮ ፈተናው ዋጋ ያለው

ባልሆነም ነበር። በዕውነትም አዳምንና ሔዋንን አሳስቶ ያንን ሥልጣን እንደወሰደ ሲያመለክት ነው።

ከአዳምና ከሔዋን ተወስዶ የነበረው መንፈሳዊ ሥልጣን በክርስቶስ ኢየሱስ በሁለተኛው አዳም እንደተመለሰልን አዲስ ኪዳን ይነግረናል ዮሐ. 1፥12፤ ሉቃ. 10፥19፤ ሮሜ 5፥12-17።

## ስለ ሰንበት ዕረፍት

በዘፍ. 2፥3 እግዚአብሔር በሰባተኛው ቀን ከሥራው ሁሉ እንዳረፈ እናነባለን። ለእኛም የህፍረትን ምሳሌ እንደተወልን የእግዚአብሔር ቃል ከዕብ. 3፥18 እስከ ዕብ. 4፥11 ያስተምረናል።

## የሰው አፈጣጠር

- ከምድርም ከሰማይም ነው (አፈርና የእግዚአብሔር እስትንፋስ)፤ ዘፍ. 2፥7
- የሚያስፈልገው ሁሉ ተሰጠው፤ ዘፍ. 2፥8-14
- እግዚአብሔር ከእርሱ በላይ መሆኑን እንዳይዘነጋ ልጓም ተደረገለት፤ ዘፍ. 2፥15-17
- ረዳት ተሰጠው ዘፍ. 2፥18-25

እኛም፤

- ምድራዊም ሰማያዊም ነን፡ -(ሥጋም መንፈስም) (2ቆሮ. 4፥7)
- ለህይወትና እግዚአብሔርን ለመምሰል የሚሆነው ነገር ሁሉ ተሰጥቶናል። (2ጴጥ. 1፥3)
- ሁሉ ቢፈቀድም ሁሉ የሚያንጽ አይደለም (1ቆሮ. 6፥12)
- አንዳችን በሌላችን ረዳት ሆነን ተሰጥተናል። (1ቆሮ 12፥21-25)

## ዘፍ. 3 - ውድቀት

ሰይጣን ሄዋንን ሲያታልላት በመጀመሪያ ጆሮዋን፣ ቀጥሎም ዓይኗን በሦስተኛም የሥጋ ምኞቷንና ፈቃድዋን አገኘ።

1. ሰይጣን በመጀመሪያ፥ የእግዚአብሔርን ቃል አጠያየቀ በውኑ እግዚአብሔር ከገነት ዛፍ ሁሉ እንዳትበሉ አዝዞአልን? አላት» በሔዋን ልብ ጥያቄ እንዲፈጠር (ቁ. 1)
2. ቀጥሎ የእግዚአብሔርን ቃል ተቃረነ፡
   «እባብም ለሴቲቱ አላት ሞትን አትሞቱም» (ቁ. 4)

3. በመጨረሻም የእግዚአብሔርን ቃል በክፉ ተረጐመ «ከእርስዋ በበላችሁ ቀን ዓይኖቻችሁ እንዲከፈቱ እንደ እግዚአብሔር መልካምንና ክፉን የምታውቁ እንድትሆኑ እግዚአብሔር ስለሚያውቅ ነው እንጂ (ቁ. 5)።

## የዘፍ. 3፥6 እና 1ኛ ዮሐ. 2፥16 ተመሳሳይነት

ዘፍ. 3፥6 «ሴቲቱም ዛፍ ለመብላት ያማረ እንደሆነ፣ ለዓይንም እንደሚያስጎመጅ፣ ለጥበብም መልካም እንደ ሆነ አየች ከፍሬውም ወሰደችና በላች ለባልዋም ደግሞ ሰጠችው እርሱም ከእርስዋ ጋር በላ።»

1ዮሐ. 2፥16 «ዓለምን ወይም በዓለም ያሉትን አትውደዱ በዓለም ያለው ሁሉ እርሱም የሥጋ ምኞትና የዓይን አምሮት ስለ ገንዘብም መመካት (የኑሮ ትምክህት በ1980 እትም) ከዓለም ስለሆነ እንጂ ከአባት ስላልሆነ ማንም ዓለምን ቢወድ የአባት ፍቅር በእርሱ ውስጥ የለም።»

- ሴቲቱም ዛፉ ለመብላት ያማረ - የሥጋ ምኞት
- ለዓይን እንደሚያስጎመጅ -የዓይን አምሮት
- ለጥበብም መልካም እንደሆነች አየች-የኑሮ ትምክህት (ስለ ገንዘብ መመካት)

### የሰይጣን ማንኛውም ፈተና ከእነዚህ ሦስተ ፡ -

በማቴ. 4፥2-11 ኢየሱስን የፈተነውም በእነዚህ በሦስቱ ነበረ ፡ -

1. ይህን ድንጋይ ዳቦ አድርገህ ብላ - የሥጋ ምኞት
2. የዓለምን መንግሥታትና ክብራቸውን አሳይቶ ወድቀህ ብትሰግድልኝ እሰጥሃለሁ አለው - የዓይን አምሮት
3. ወደ ቤተ መቅደስ ጫፍ ወስዶ «መላእክት በእጃቸው ያነሡሃል» ተብሎ ተጽፎአልና፤ የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንክ ራስህን ወርውር። - የኑሮ ትምክህት

- የሰይጣን ዋና ዓላማ የእኛን ፈቃድ ከእግዚአብሔር ፈቃድ እንዲያፈነግጥ ማድረግ (ማሹታት) ነው፡

### የእግዚአብሔር ቃል የሚሠጠን ማስጠንቀቂያ

2ቆሮ. 11፥3 «ነገር ግን እባብ በተንኮሉ ሔዋንን እንዳሳታት አሳባችሁ ተበላሽቶ ለክርስቶስ ከሚሆን ቅንነትና ንጽህና ምናልባት እንዳይለወጥ ብዬ እፈራለሁ።»

* የሰይጣን ፈተና ሁሉ የሚጀምረው ከሐሳብ ነው።

## የአዳምና ሔዋንን ውድቀት ያስገኘው ውጤት

1. ዓይኖቻቸው ለክፉ ተከፈቱ (አሳባቸው ተበላሸ)
   «ዓይኖቻቸው ተከፈቱ ዕራቁታቸውንም እንደሆኑ አወቁ።» - ቅንነት ራቃቸው (ዘፍ. 3፥7)።

2. ኃፍረት ወደ ህይወታቸው መጣ
   «ቅጠሎች ሰፍተው አገለደሙ» (ዘፍ. 3፥7)።

3. በላያቸው የነበረው ጸጋ ተገፈፈ
   «እራቁታቸውን እንደሆኑ አወቁ» (ዘፍ. 3፥7)። በፊት የእግዚአብሔር ክብር ሸፍኗቸው ነበረ። ሙሴ ከእግዚአብሔር ጋር ሲነጋገር የፊቱ ቁርበት ያበራ እንደ ነበረ።
4. ፍርሃት ወደ ህይወታቸው መጣ፡ -
   «... ፈራሁ ተሸሸግሁም» ዘፍ. 3፥10።
5. ማሳበብ- ስህተትን አለመቀበል ተጀመረ (ዘፍ. 3፥12-13)።
   አዳም፣ «ከእኔ ጋር እንድትሆን የሰጠኸኝ ሴት እርስዋ ከዛፉ ከሰጠኝና በላሁ» አለ። «... ሲቲቱም አለች፡ - እባብ አሳተችኝ በላሁ።»
6. ከእግዚአብሔር ተለዩ፡ - መንፈሳዊ ሞት
   «ከአምላክ ፊት በገነት ዛፎች መካከል ተሸሸጉ» ዘፍ. 3፥8
7. የሥጋም ሞት ለሰው ሁሉ ደረሰ (ዘፍ. 5፥5፣ ሮሜ 5፥12)
8. ምድር ተረገመች
   «... ምድር ከአንተ የተነሣ የተረገመች ትሁን» ዘፍ. 3፥17።

## ይህ ታላቅ ውድቀት በታላቅ ተስፋ ይደመደማል

«በአንተና በሴቲቱ መካከል በዘርህና በዘርዋም መካከል ጠላትነትን አደርጋለሁ እርሱ ራስህን ይቀጠቅጣል አንተም ሰኮናውን ትቀጠቅጣለህ» (ዘፍ. 3፥15)። በዚህ ጥቅስ «እርሱ እና «የሴቲቱ ዘር» የተባለው ከቅድስት ድንግል ማርያም የተወለደው ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው (ገላ. 4፥4 ኢሳ.

9÷6፤ ኢሳ. 7÷14)። የዲያብሎስን ራስ (ሥልጣን) እንደቀጠቀጠ ቆላስይስ 2÷14-15 ይገልጻል።

ምንም ዓይነት ውድቀት በህይወታችን ቢመጣ እግዚአብሔር ሁልጊዜ ውድቀታችንን በተስፋ ያነሳል። በቅጣቱም ሆነ በቁጣው ውስጥ እንኳን የእግዚአብሔር ምህረትና ተስፋ አለ።

## <u>የኃጢአት እድገት</u>

1. <u>አዳምና ሔዋን</u> የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ተላለፉ (ዘፍ. 3)
2. <u>ቃየን</u> ወንድሙን አቤልን በቅንአት ገደለው (ዘፍ. 4÷1-8)
3. <u>ላሜሕ</u> (የቃየን አምስተኛ ትውልድ) ነፍሰ ገዳይ እንደነበረ እናነባለን።
   «እኔ ጐልማሳውን ለቁስሌ ብላቴናውንም ለመወጋቴ ገድዬዋለሁና፤ <u>ቃየንን ሰባት እጥፍ</u> ይበቀሉታል፤ <u>ላሜሕን ግን ሰባ ሰባት እጥፍ</u>።» ዘፍ. 4÷23-24 - ኃጢአት እያደገ ሲሄድ
4. <u>ሰው ሁሉ በኃጢአት ተበከለ</u> - «እግዚአብሔርም የሰው ክፋት በምድር ላይ እንደበዛ፥ የልቡ አሳብ ምኞትም ሁልጊዜ ፈጽሞ ክፉ እንደሆነ አየ» <u>ዘፍ. 6÷5-6</u>።

## የውኃ ጥፋት
### (ዘፍ. 6-8 የእግዚአብሔር ፍርድ)

- የሰው ክፋት በምድር ላይ ስለበዛና ምድር በግፍ ስለተሞላች እግዚአብሔር የሰው ልጆችን ሁሉ (ከኖኅና ከቤተሰቡ በስተቀር )እንዳጠፋ እናያለን።

ከዚህ ክፍል የምንማረው

1. በዙሪያችን ያሉ ሁሉ በኃጢአት ቢበከሉና አንድም እንኳን እግዚአብሔርን የሚፈራ ባይኖር እኛ እንደ ግለሰብ እግዚአብሔርን በመፍራትና በጽድቅ (እንደ ኖኅ) መኖር እንችላለን <u>«ኖኅ ግን</u> በእግዚአብሔር ፊት ሞገስን አገኘ» (ዘፍ.6÷8)

2. እግዚአብሔር እርሱን <u>የሚያመልኩትንና የሚፈሩትን እንደሚያድንና ዓመፀኞችን ደግሞ በፍርድ እንደሚያጠፋ</u> 2ጴ. 2÷4-10 «እንግዲህ የእግዚአብሔርን ቸርነትና ጭከና ተመልከት» ሮሜ 11÷22።

3. የኖህና የጥፋት ውኃ ታሪክ ለመጨረሻው ዘመን ምሳሌ ነው። የኖኅ ዘመን እንደ ነበረ የሰው ልጅ መምጣት እንዲሁ ይኖራልና ...» ማቴ. 24፥37-42።

## የባቢሎን ግንብ

(ዘፍ. 11፥1-9)

ይህ ክፍል፤

1. የሰውን ትዕቢትና ትምክህት ያሳያል፤
ዘፍ. 11፡4 «.. በምድር ላይ ሳንበተን ስማችንን እናስጠራው።»
የእግዚአብሔርን ስም ሳይሆን የራሳቸውን ስም ለማስጠራት ፈለጉ። እግዚአብሔር ለአብርሃም (ዘፍ.12፡ 2) «ስምህን አከብረዋለሁ ይለዋል። በ1ዜና 17፡8 ደግሞ ለዳዊት «... በምድርም እንዳሉ እንደ ታላላቆች ስም ለአንተ ስም አደርጋለሁ» ይለዋል እግዚአብሔር ስማችንን ሲያከብረው እንጂ እኛ ራሳችንን ስማችንን ማስከበር የለብንም።

2. ሰው ለክፉ እንኳን በአንድ ሐሳብ ከተነሣ የሚያቅተው እንደሌለ ያሳያል፤
ዘፍ. 11፡6 «እግዚአብሔርም አለ፡ - እነሆ እነርሱ አንድ ወገን ናቸው፥ ለሁለም አንድ ቋንቋ አላቸው፤ ይህንም ለማድረግ ጀመሩ አሁንም ያሰቡትን ሁሉ ለማሠራት አይከለከሉም

አንድነት፥ ለክፉ (እግዚአብሔር ለሌለበት) ነገር እንኳን መካናወን የሚከተ ከሆነ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ለሆነ መልካም ነገር አንድ ስንሆንማ ምን የሚያቅተን ነገር ይኖራል (መዝ. 132፥133)።

3. እግዚአብሔር ሁልጊዜ የሰውን ትዕቢት እንደሚቃወምና የትዕቢትን ሥራ እንደሚያፈርስ ያሳያል። «ኑ እንውረድ አንዱ የአንዱን ነገር እንዳይሰማው ቋንቋቸውን በዚያ እንደባልቀው እግዚአብሔር ከዚያ ምድር ሁሉ በተናቸው ከተማይቱንም መሥራት ተዉ» (ዘፍ. 11፡7-8)።

«እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን ይቃወማል ለትሑታን ግን ጸጋን ይሰጣል» ያዕ. 4፡6።

- ትዕቢት ውድቀትን ትቀድማለች።

4. ይህ በብሉይ ኪዳን የተከሰተ ታሪክ በአዲስ ኪዳን ዘመን በሥውር ለምትሰራው ለታላቂቱ ባቢሎን ማለትም በሰይጣን መንፈስ

እየተመራች የእግዚአብሔርን መንግሥት የምትገዳደር ምሳሌ ነው (ራዕ. 16፡19 17፡ 1-19፡3)።

**በብሉይ ኪዳን ውስጥ ያሉ ሰባት የእግዚአብሔር ሰዎች**
**(Explore The Book, J. Sidlow Baxter-Page 65)**

1. አቤል ዘፍ. 4፥4 ዕብ. 11፥4 (መንፈሳዊ ፍላጎት) የእግዚአብሔርን ነገር የሚፈልግ ደስ የሚያሰኝ መስዋዕት አቀረበ።

2. ሄኖክ፡ - ዘፍ. 5፥22-24፤ ዕብ. 11፥5-6 (መንፈሳዊ ምርጫ) «ሄኖክ አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር አደረገ... ሄኖክም አካሄዱን ከአግዚአብሔር ጋር ስላደረገ አልተገኘም እግዚአብሔር ወስዶታልና» ዘፍ. 5፥22-24።
   ዕብ. 11፥6 «...ሳይወሰድ እግዚአብሔርን ደስ እንዳሰኘ ተመስክሮለታልና»
   እኛም በአካሄዳችን የእግዚአብሔርን መንገድ መምረጥ አለብን።
3. ኖኅ፡ - ዘፍ. 9- (መንፈሳዊ ተሐድሶ)

   ኖኅ ከአሮጌው፥ በውሃ ከጠፋው ዓለም ወደ አዲሱ ዓለም የተሸጋገር ሰው ነው። አዲስ ቃል ኪዳንን የተቀበለ ሰው ነው።

   - የኖኅ ህይወት የደኅንነት (የተሐድሶ) ምሳሌ ነው። «ጥቂቶቹ ማለት ነው። ስምንት ነፍስ በውሃ የዳኑበት መርከብ ሲዘጋጅ የእግዚአብሔር ትዕግስት በቆየ ጊዜ ቀድሞ አልታዘዙም። ይህ ውሃ ደግሞ ማለት ጥምቀት ምሳሌው ሆኖ አሁን ያድነናል» 1ኛ ጴጥ. 3፥20-21
   - መርከቡ የክርስቶስ ምሳሌ ነው።
     «ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው አሮጌው ነገር አልፎአል እነሆ ሁሉም አዲስ ሆኖአል» (2ቆሮ. 5፡17)።

4. አብርሃም፡ - ዘፍ. 15፡6 የእምነት ህይወት (ጉዞ) «አብርሃምም እግዚአብሔርን አመነ ጽድቅም ሆኖ ተቆጠረለት (ሮሜ 4፥3)። «ጻድቅ በእምነት ይኖራል» (ሮሜ 1፥17)

5. ይስሐቅ ዘፍ. 21፡1-3 የተስፋ ቃል ልጅ ለአባቱ ፍጹም ታዛዥ የነበረ ልጅ ራሱን ለመስዋዕትነት እስኪሰጥ ዘፍ. 22፡1-12
   - (የልጅነትን ሥልጣንና ህይወት ያሳያል) «እንግዲህ እንደ ተወደዱ ልጆች እግዚአብሔርን የምትከተሉ ሁኑ» ኤፌ. 5፡1

«የእግዚአብሔር ልጆች ተብለን ልንጠራ አብ እንዴት ያለውን ፍቅር እንደሰጠን እዩ፤ እንዲሁም ነን» (1ኛ ዮሐ. 3፥1)።

«ለተቀበሉት ሁሉ ግን በስሙ ለሚያምኑት የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው» (ዮሐ. 1፥12)።

6. ያዕቆብ ዘፍ. 29፡15-30 (የአገልግሎትና የበረከት) ህይወት ለሁለቱ ሚስቶቹ ለራሄልና ለልያ 14 ዓመት ሲያገለግል እናያለን።

- «ካልባረከኝ አልለቅህም» (ዘፍ. 32፡26) በማለት ከእግዚአብሔር ጋር በጸሎት የታገለ ሰው ነው። አንዳንድ ጊዜ አካሄዱ በራሱ ብልጠት በመመራት ቢሆንም ልቡ ከሥጋዊ ነገር ይልቅ መንፈሳዊ ነገር ላይ ያተኮረ ነው። ለብኩርና ሲል ምግብን ተወ። ኤሳው ግን፡ - ለምግብ ሲል ብኩርናውን ተወ።
- የእግዚአብሔር ቃል እኛንም በ1ቆሮ. 15፡58 «ድካማችሁ በጌታ ከንቱ እንዳይሆን አውቃችኋልና የምትደላደሉ የማትነቃነቁ <u>የጌታም ሥራ የሚበዛላችሁ ሁኑ</u>» ይለናል። በተጨማሪም፤ በዕብራውያን 12፡16፣ ማንም፤ «ስለ አንድ መብል በኩርነቱን እንደ ሸጠ እንደ ኤሳው እንዳይሆን ይላል

7. ዮሴፍ፡ - ዘፍ. 37፡- ዘፍ. 50 የመከራና የክብር ህይወት
   ዮሴፍ በህይወት ዘመኑ <u>ታላቅ መከራና ታላቅ ክብር</u> የተቀበለ ሰው ልጅ ነው።

- የልጅነትና የአገልግሎት ህይወት ብቻ ሳይሆን ለክርስቶስ መከራን ልንቀበል ደግሞ ተጠርተናል። «... ስለ እርሱ (ስለ ክርስቶስ) መከራ ደግሞ ልትቀበሉ እንጂ በእርሱ ልታምኑ ብቻ አይደለም» (ፊል. 1፥29)።

## <u>መከራና ክብር</u>

በትዕግስት በምናልፍበት መከራ ጥልቅነት መጠን ወደፊት የምናገኘው ክብር ያን ያህል ታላቅ ይሆናል።

«ልጆች ከሆንን ወራሾች ደግሞ ነን፣ ማለት የእግዚአብሔር ወራሾች ነን፣ አብረንም ደግሞ እንድንከበር አብረን መከራ ብንቀበል ከክርስቶስ ጋር አብረን ወራሾች ነን። ለእኛም ይገለጥ ዘንድ ካለው ክብር ጋር ሲመዛዘን የአሁኑ ዘመን ሥቃይ ምንም እንዳይደለ አስባለሁ» (ሮሜ 8፡17-18)።

«.. ቀላል የሆነ የጊዜው መከራችን ወደር የሌለውን እጅግ ታላቅ የሆነ ዘላለማዊ ክብር ያስገኝልናል» (2ቆሮ. 4፡17-18)፡፡ ስለዚህ ነው ያዕቆብ «... ልዩ ልዩ ፈተና (መከራ) ሲደርስባችሁ እንደ ሙሉ ደስታ ቁጠሩት» የሚለን (ያዕቆብ 1÷3)፡፡

የዮሴፍ ህይወት የኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ ነው፡፡

<u>የዮሴፍ ህይወት በሦስት ይከፍላል</u>፡፡

፩. ለአባቱ ተወዳጅ ልጅ ነበረ፡ -
፪. መከራን የተቀበለ ታማኝ አገልጋይ ነበረ፡ -
፫. በሁሉ ላይ ከፍ ያለ ታላቅ ልዑል ሆነ፡፡

፩. ተወዳጅ ልጅ

- ዮሴፍ ለአባቱ በጣም ተወዳጅ እንደነበረ የእግዚአብሔር ቃል ይነግረናል፡፡
- ኢየሱስም በአብ ዘንድ የተወደደ አንድያ ልጅ እንደሆነ እናያለን፡፡

፪. በመከራ ውስጥ የጸና ታማኝ አገልጋይ፣

- ዮሴፍ በወንድሞቹ ተጠልቶና ተሸጦ ወደ ግብጽ ከወረደ በኋላ በጶጢፋር ቤት ታማኝ አገልጋይ ነበረ፤ ባላደረገው ኃጢአት እሥር ቤት ከገባም በኋላ በእስር ቤት እሥረኞቹን ሲያገለግል ነበር፡፡
- ኢየሱስም በጊዜው በነበሩበት አይሁዳውያን ተንቆና ተጠልቶ ቢሰቀልም የአባቱን ፈቃድ ሁሉ በታማኝነት ፈጽሞ «በምድር ላይ የሰጠኸኝንም ሥራ ፈጽሜ አከበርኩህ» (ዮሐ. 17÷4) በማለት ሲጸልይ እንሰማለን፡፡
  ሁለቱም ሌሎችን ለማዳን መከራን ተቀበሉ፡፡

፫. በሁሉ ላይ ከፍ ከፍ ያለ ታላቅ ልዑል፤

- ዮሴፍ ያንን ሁሉ መከራ በትዕግሥት ከተቀበለ በኋላ የግብጽ ንጉሥ (ፈርዖን) ከሁሉ በላይ ከፍ ከፍ አደረገው፡፡
- በፊልጵስዩስ 2÷6-11 እግዚአብሔር አብ ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን እንዴት ከፍ ከፍ እንዳደረገው ከስሞች ሁሉ በላይ የሆነውን ስም እንደሰጠው እናያለን፡፡

ከዚህ የምንማረው፤

- ለእግዚአብሔር የተወደደ ልጅ ከሆንን ኤፌ. 5፥1
- ለእግዚአብሔር ታማኝ አገልጋይ ከሆንን
- እግዚአብሔር ከፍ ከፍ እንደሚያደርገን ነው (1ጴጥ. 5፥6)።

## ምዕራፍ ሁለት፣ ጥያቄዎች

1. ዘፍጥረት ነገሮችን ሁሉ ሥርና መሠረት የያዘ ነው ሲባል ምን ማለት ነው?

2. ዘፍጥረትና ራእይ የሚመሳሰሉበትን ሁለት ነጥቦች፤ የሚለያዩበትን ደግሞ ሦስት ነጥቦች ጥቀስ።

3. በዘፍ. 1፥1 በዘፍ. 1፥2 መካከል አለ የሚባለውን ልዩነት አብራራ።

4. የዘፍጥረት መጽሐፍ የሚከፋፈልበት አራት ድርጊቶችና አራት ግለሰቦች ምን ምን ናቸው።

5. በቁጥር 4 የተጠየቁትን ጨምሮ፤ በዘፍጥረት ውስጥ ያሉትን ሰባት የእግዚአብሔር ሰዎች ከጠቀስክ በኋላ እያንዳንቸው ምን እንደሚያመለክቱ ግለጽ።

6. ሰይጣን ሔዋንን ሲፈትናት በሦስት ደረጃ እንደሆነ እናስተውላለን። እነዚህን ሦስት ደረጃዎች ግለጽ።

7. በዘፍጥረት ምዕራፍ 3 ውስጥ የአዳምና የሔዋንን መተላለፍ ካስገኘው ውጤት አራቱን ጥቀስ።

8. ዮሴፍና ኢየሱስ የሚመሳሰሉበትን ሦስት ነገሮች አብራራ።